EthioLion

# ኢትዮጵያዊነትን የጥቃት ሰለባ ያደረገው የጎሳ ፌዴራሊዝምና የወያኔ የአፓርታይድ ሥርዓት።

ባለፉት ሃያ አንድ ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ በጎሳ ማንነትና ቋንቋ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካዊና የአስተዳደር ስርዓት ተዘርግቷል። ይህ የወያኔ ስርዓት የሃገሪቱ መተዳደሪያ ያደረገው ህገ መንግስት “የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ስልጣን ባለቤት የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ናቸው” ይላል። በመሆኑም ህገ መንግስቱ መብትን የሚያጎናጽፈው ለእነዚህ “ብሄሮች፤ ብሄረሰቦችና ህዝቦች” ለሚባሉት ስብስቦች ነው። በመሆኑም በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የዜግነት መብት የጎሳ ማንነትን በመንተራስ በክልል ድንበር የተገደበ እንጂ ጎሳ-ዘለል የሆነ ኢትዮጵያዊ ማንነትን የሚያንጸባርቅ አይደለም። ይህ የጎሳ ስርዓት በፈጠራቸው የጎሳ ክልሎች ውስጥ ሁለት ዓይነት ኢትዮጳያውያን ዜጎችን ፈጥሯል። ይህም ባንድ ወገን “ነባር ጎሳዎች” የሚባሉትንና “መጤ ጎሳዎች” የሚባሉ ኢትዮጵያውያንን ፈጥሯል። ከክልላቸው ውጭ መጥታችሁ አላግባብ ትኖራላችሁ እየተባሉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በጭንቀትና በሰቀቀን መኖር ከጀመሩ ሃያ አንድ ዓመታት ተቆጥረዋል። ይኸ ግን የዛሬዎችቱን ገዚዎች ተከታዮች አይመለከትም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በማጂ ቤንች ዞን በጉራ ፈርዳ ወረዳ እየተደረገ ያለው የአማራውን ጎሳ ተወላጆች ከአካባቢው የማጽዳት ዘመቻ የዚህ የጎሳ ፌዴራሊዝም ነጸብራቅ ነው። የጎሳ ፌዴራሊዝም ኢትዮጵያዊ ዜግነትን የማያውቅ፡ የማያስጠብቅና የማያረጋግጥ ስርዓት ነው።

ይህ የጎሳ ፌዴራሊዝም በሀገራችን ውስጥ ሰላም፤ መተሳሰብና ፍቅርን ከማምጣት ይልቅ መቃቃር፤ መራራቅን፤ የእርስ በርስ ጥርጣሬና ጥላቻን አስከትሏል። ከዚያም አልፎ ይህ በጎሳ ማንንነትና ልዩነት ዙሪያ የተቃኘው የወያኔ የጎሳ ፖለቲካ ስርዓት ከስልሳ በላይ ለሆኑ የርስ በርስ ግጭቶች መንስዔ ሆኖ ቆይቷል። ዛሬ እየተካሄደ ያለው የአማራን ጎሳ ከቤንች ማጂ ዞን የማጽዳት ዘመቻ ሆን ተብሎ በእውቅ በወያኔ መሪዎች ከአዲስ አበባ በሚሰጥ መመሪያ እንደሚከናወን ግልጽ ነው። ወያኔ ሲፈጠር ጀምሮ በጠላትነት የፈረጀው የአማራ ጎሳ ባለፉት ሃያ አንድ አመታት በግልጽ ሰፊ የፕሮፓጋንዳና ስሙን ጥላሸት የመቀባት ዘመቻ ከተደረገበትና በአውሬነትና በአጥፊነት እንዲታይ ከተደረገ በኋላ እነሆ ዛሬ በግልጽ እንደ አውሬ እየታደነ በመሳደድ ላይ ይገኛል። በመጪው ሳምንት እሁድ አፕሪል ሃያ ዘጠኝ 2012 እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ከሰዓት በኋላ ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው የቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ህዝባዊ ስብሰባ ይደረጋል። ስብሰባው ከሰአት በኋላ ከቀኑ ስምንት ሰአት ላይ ይጀመራል።

**Location: St. Gabriel Ethiopian Orthodox Church**
**2601 Evarts Street, North East 20018 DC**
**Date: Sunday, 29th April 2012**
**Time: 2:00 PM Eastern**

በህዝባዊ ስብሰባው ላይ፤

፩ - በቅድሚያ ክቡር አምባሳደር እምሩ ዘለቀ ሞረሽ ስለተባለው ማህበራዊ እንቅስቃሴና ዓላማው ገለጻ ያደርጋሉ።

፪ - በመቀጠልም የሚከተሉትን ነጥቦች ያካተተ በፓወር ፖይንት (power point) የተደገፈ ንግግር ሆላንድ ሃገር ነዋሪ በሆኑት በዶክተር አሰፋ ነጋሽ ይቀርባል።

በእለቱም ዶክተር አሰፋ ነጋሽ የሚከተሉትን ጉዳዮች በማንሳት ሃሳባቸውን ያካፍላሉ።

- የኢትዮጵያን ማንነት የጥቃት ዓላማ ያደረገው የወያኔ የጎሳ ፌዴራሊዝም መነሻውና መድረሻው ምንድነው?

- በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ያለው ህገ መንግስት ኢትዮጵያዊ ዜግነትን ያረጋግጣልን?

- የአማራው ህዝብ ለምንና እንዴት ለዚህ ለአሁኑ ጥቃትና መፈናቀል ሊጋለጥ ቻለ?

- ከዚህ የጎሳ ማጽዳት ዘመቻ በፊት ቀስ በቀስ ለረጅም ጊዜ የተካሄደው በአማራው ህዝብ ላይ ያነጣጠረው የስነ ልቦና ጦርነት ምን ዓይነት መልኮች ነበሩት፤ ዛሬስ ምን ይመስላል?

- ችግራችን መለስ ዜናዊ ወይስ አክራሪው የትግራይ ብሄረተኛነት ነው?

- የወያኔ ስርዓት የፈጠረው የአፓርታይድ ስርዓት ያስከተላቸው የተዛቡ የክልሎች እድገት በንፅፅር የሚያሳዩ ስታተስቲካዊ አሃዞችና መረጃዎች ለስብሰባው ታዳሚዎች ያቀርባሉ።

- ሐገራችን ወደት እየሄደች ነው? ከእንግዲህ ምን ልናደርግ ይገባል በሚለው ጉዳይ ላይ ለውይይት የሚረዱ ጠቋሚ ሃሳቦችን ያቀርባሉ።

**Ethiopia Will Prevail!**